## ምዕራፍ አንድ
## የምሥጢረ ቁርባን ጠቃሚነት

ምልክቶች ብዙ ጊዜ በቃል መግለጫ የማይገኝለትን የምሥጢርን ጥልቅነትና እምነት ይሰጣሉ። መንፈስ አይደለንም ሥጋ ያለን መንፈስ እንጂ። ብዙ ጊዜ በቃል ብቻ ሳይሆን ግዙፉን (ማቲሪያል) በሆኑ ምልክቶች እውነትን ደኅና አድርገን መረዳት እንችላለን። የፈጠረውን ባሕርያችንን ሊያጠፋ የማይወድ አምላክም ወደሱ ስንቀርብ እንዲሁ እንድናደርግ ያሰተምረናል። እነዚህም ምልክቶች ዕጥፍ ድርብ አሳብ አላቸው። እነሱ ግዙፉን ሲሆን ግዙፍ ለሆነው ሰው ምሥጢርን ያስረዳሉ። ደግሞ በሚሠራባቸው ሰው ላይ የማነጽ ሥልጣን አላቸው። ዘላለማዊነትን በሚያስረዱ በእነዚህ ምልክቶች መላልሰን በእውነት ብንሠራባቸው የዘላለም ቤተ ሰቦች ለመሆን እንደርሳለን።

ነገር ግን ከነዚህ ምልክቶች አንዳንዶቹ ልዩ ከሆነ ዓይነትና ኃይል የተገኙ ናቸው። እነሱም የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ናቸው። ለሚያመለከቱትም ፍጻሜ ያስገኛሉ። የጥምቀት ሥርዓት በምልክትነት ሀብታም ነው። አነስተኞች ምልክቶች ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ጭፍሮች እንደ ሆኑ እንዲሁም ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ሁሉ ከሁሉ የበለጠው የምሥጢረ ቁርባን ጭፍሮች ናቸው።

ይህ ለክርስቲያን ሕይወት ዋና መገናኛ ምልክት ነው። ምክንያቱም ከዚህ ሌሎች መሥዋዕቶች ሁሉ ወሰን ወደሌለው ወደ ክርስቶስ መሥዋዕትን ስለ ተሰበሰቡና የራሱን መሥዋዕትና በሚጠራው ዓለም ላይ የፈሰሰውን አምላካዊ ደም በመቀበል ኃጢአትን የተሸከመ የሰው ዘር ወደ ላይ መጮህ የተፈጸመበትና ድኅነት የተገኝበት ስለ ሆነ ነው። ምሥጢረ ቁርባን የመስቀል ምልክት እንደ ሆነ በእውነት ተነግሮዋል።

ከሰው ስህተት በኋላ ሁለት ነገሮች ሆኑ እነዚህም እንደ ገና ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ መመኘትና ወደርሱ ለመድረስ አለመቻል ናቸው። ግን እነዚህ የሚቻሉ ሆኑ። ምክንያቱም በመስቀል መሥዋዕትና መስቀልም ዘወትር ስለሚዘጋጅና በሥጋ ወደም እንደሚሠራ ስለ ተደረገ በርሱም ለዓለም መሥዋዕት ለመሆን የክርስቶስ መሥዋዕትነት ኀይልና መለኮታዊነት ሁሉ ለያንዳንዱ ሰው ነፍስ ከዚያም በጠቅላላው ወደ ሰው ፍጥረት ወገን ስለ ደረሰና ድካም ተወግዶ ተስፋ ስለ ተፈጸመ ነው።

ይህ የሃይማኖት ሥርዓት ወደ መጀመሪያው የሃይማኖታችን መገኛ ይመልስናል እርሱም ከአዲስ ኪዳን የተቀደመ ነው። በማናቸውም ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ከመኖሩ አስቀድሞ ከቶውንም ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ይሠራበት ነበር። ከመጀመሪያው ጰራቅሊጦስ ወዲህ ክርስቲያኖች ከቃል ይልቅ ጥብቅና ግልጥ በሆነ ሥርዐት የጌታችንን ስለኛ በመስቀል መሞት ሳያሳዩ አንድ እሑድ ምናልባትም አንድ ቀን እንኳን አልታለፈም። ወደፊትም እርሱ እስቲመጣ ያሳያሉ።

1. ቅዱስ ቁርባን ከሌሎች ምሥጢራት ሁሉ የበለጠ እንደ ሆነ ታውቋል። በዚህ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ራሱን ቅዱስ ኅብስት አድርጎ ስለ ሰጠን “እኔ ነኝ። ከሰማይ የወረደ ሕያው ኅብስት ማንም ከዚህ ኅብስት የበላ ለዘለዓለም ይኖራል ይህም ኅብስት እኔ ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው ሥጋዬ ነው ብሏል” (ዮሐንስ 6:56)
2. በርሱ ከጌታችን ጋር አንድ ስለሆነ እርሱ በእኛ ይኖራል እኛም በአርሱ እንኖራለን። ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ ብሏል (ዮሐንስ 6:56)
3. በዚህ ዓለም ያለው ሁኔታችን እንደ ሚመሰክረው ወደ አምላክ ፊት ለመቅረብ በዚህ ከሁሉ የቀረበ መንገድ ስላለን ነው።

የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያኖች ለዚህ ምሥጢር ምንም እንኳ ከሁሉ የበለጠ ክብር ቢሰጡ ከወገኖቻቸው ብዙዎች ባካሄዳቸው የዚህን ክብር ምልክት ትንሽ ስንኳ አያሳዩም ከነሱ ብዙዎች ሥጋውን ደሙን መቀበል በጣም አስፈላጊ መሆኑን እያመኑ ስለ መቀበሉ ብዙ ጊዜ አያስቡትም። ከሚቀበሉትም ብዙዎች እንዲያው ለልማድ ያህል ይቀበሉታል እንጂ ከሁሉ የበለጠ አስፈላጊ መሆኑን አያውቁም። ቤተ ክርስቲያንንም በጣም ቢያከብሩዋትም ልዩ ልዩ አገልግሎቷንም ሳያስታጉሉ ቢፈጽሙና ሥርዐቱን ሁሉ በጥንቃቄ ቢጠብቁም ቅሉ ሥጋውን ደሙን አለመቀበላቸውን ባየሁ ጊዜ በጣም ገረመኝ። በአዲስ አበባ በብዙ ቤተ ክርስቲያኖች በቅዳሴ ጊዜ ስለ ነበርሁ ሥጋውን ደሙን የተቀበሉ እነዚያው ቀዳሲያኖችና ጥቂት ወራት የሆናቸው ሕፃናት ብቻ መሆናቸውን ተመለከትሁ። የኢትዮጵያ ሰው አንድ ጊዜ በጥምቀት ሁለተኛ ጋብቻው በቤተ ክርስቲያን የሆነ

አንደ ሆነ በጋብቻ ጊዜ ወይም በጽኑ ሕመም በታመመ ጊዜ ካልሆነ በቀር ከቶ ሥጋውን ደሙን አይቀበልም ይባላል።

ይህ በጣም ዋና ነገር ስለ ሆነ የተወደደችዋ ቤተ ክርስቲያን በእውነት እንድትታደስ የተከበሩ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች በጥበብ እንዲያስቡበት በትሕትና አሳስባለሁ። ደግሞ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ይህንን ታላቅ ስሕተት እንዲያርሙ እለምናለሁ።

## ምዕራፍ ሁለት
## ሥጋውን ደሙን መቀበል የሚገባን ስለ ምንድር ነው?

ልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያኖች ስለ ሥጋው ደሙ በእምነት ቢለያዩ እንኳ መንፋሳዊ ሕይወትን ለማጠንከር ሥጋው ደሙ በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ አንድም ሳይቀር ሁሉም ይተባበራሉ። በርሱ የምንቀበላቸውን ልዩ ልዩ በረከቶች ለማግኘት ሥጋውን ደሙን መቀበል ይገባናል።

1. በርሱ ታላቁን ስጦታ የኃጢአትን ሥርየት እንቀበላለን። ምሥጢረ ቁርባንን በመሠረተ ጊዜ ራሱ ያረጋገጠው ይህ ነው። ጽዋውንም ተቀብሎ አመሰገነ ይህ የሐዲስ ሥርዓት ኃጢአትን ለማስተስረይ ስለ ብዙ ሰዎች የሚፈስ ደሜ ነውና ሁላችሁ ከዚህ ጠጡ ብሎ ሰጣቸው (ማቴ-26:27-28) ሥጋውን ደሙን አክብሮ በመቀበል ሃይማኖት ይመሠረታል። ንስሐ ለሚገባውም ሰው የኃጢአት ሥርየት ይረጋገጥለታል ክርስቶስን የበለጠ ቀርቦ ለመከተልና በበለጠ እምነት እርሱን ለማገልገል ነፍስ ኀይል አግኝታ ትበረታለች።
2. ክርስቶስ በመስቀል ካስገኘው ድል ተካፋዮች እንሆናለን። የሥጋው መቆረስና የደሙ መፍሰስ ድል አድራጊውን የሕይወቱን መታዘዝ ለመፈጸም ፍቅር ያማይሸነፍ መሆኑን ለማሳየት "የስንዴ ቅንጣት ከምድር ካልወደቀችና ካልሞተች ለብቻዋ ትኖራለች የሞተች እንደሆን ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች(ዮሐ.12:24) ያለውን የራሱን ቃል ለማረጋገጥ ነው። ሥጋው ደሙ የዚህ ድል ምልክት ነው። ግን ይህ ብቻ አይደለም ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ ለራት ተካፋይ ሆነ ይህ ያለጥርጥር የሚያሳየው ደቀ መዛሙርቱ ከድሉ ተካፋይ እንዲሆኑ የርሱ አሳብ መሆኑን ነው። ጀስቲን ማርቲር በሁለተኛው መቶ ዓመት የነበረ በጻፈውና የቀደሙት አባቶች በጻፏቸው በሌሎች ጽሑፎች ምሥጢረ ቁርባን የድል ምልክት ሆኖ የቁዮ ለመሆኑ ማስረጃ እናገኛለን። ከትሪፋስ ጋራ ስለ ምሥጢረ ቁርባን ሲጻጻፍ ከማናቸውም ኃጢአት በነፍስ ለነሱ መከራ ለመቀበሉ መታሰቢያና ከነበርንበት ክፋት ነጻ ስለ አወጣንና በፈቃዱ መከራ በተቀበለ በርሱ የቀደሙትን ገዢዎች ድል ስላደረገ ለእግዚአብሔር ምስጋና እንድናቀርብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የወሰነው በዓል መሆኑን ይናገራል። ክርስቶስን በሥጋው ደሙ ስንገናኘው ስለራሱ ሁለት እውነት የሆኑ ነገሮች እንድናይ ያደርገናል። ባየናቸውም ጊዜ ሁሉን ነገር  አዲስ ያደርጉልናል። ራሱ ያስገኘውን ድል ያሳስበናል። እኛም ደግሞ ድል አድራጊዎች ለመሆን እንድንችል በዚያው ጊዜ የትንሣኤውን ኀይል እንድንካፈል ያደርገናል። ፋሲካ የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ባርነት የወጡበትን ቀን ለማክበር የተሠራ የምስጋና በዓል ነው። የጌታም ራት ከኃጢአት ባርነት በመንፈስ ነጻ ስለ ወጣን ምስጋና ማቅረቢያ ነው። "አለቆችም ሥልጣናትንም በገፈፈ ጊዜ በግልጥ አላያቸው። በርሱም አስፈራቸው።" (ቆላ. 2:15) እያልን ጸጋውን እናከብረዋለን። መልአከ ሞት እንኳን ለክርስቶስ መስቀል ይገባል። ሞት በሥጋው ደሙ እሾሁን ተቀምቶ ሥልጣኑን ተገፎ እናየዋለን። ለእግዚአብሔር የተሠዋው የክርስቶስ ሥጋና ደም የሞትን ጨለማ አስወግዶ የዘለዓለም ሕይወት በር አደረገው።
3. ለነፍስ ምግብ እናገኛለን። "ኢየሱስም አላቸው። የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። ወደ እኔም የሚመጣ አይራብም። የሚያምንብኝም ለዘለዓለም አይጠማም። ከሰማይም የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። ማንም ከዚህ እንጀራ የበላ ለዘለዓለም ይኖራል። ይህም እንጀራ እኔ ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው ሥጋዬ ነው። ሥጋዬ የእውነት መብል ደሜም የእውነት መጠጥ ነውና። (ዮሐ. 6:35 51 55) ለሰውነት ምሉ ምግብ ማግኘት እንደሚያስፈልግ እንዲሁም ለነፍስ ሙሉ ምግብ ማግኘት ያስፈልጋታል።
4. በክርስቶስ እንኖራለን እርሱም በኛ ይኖራል ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ በኔ ይኖራል እኔም በርሱ እኖራለሁ።(ዮሐ. 6:56) የክርስቶስ የራሱ ሥጋና ደም ይህ ነው። ይህን መብላትና መጠጣት በጣም

የቀረበ አንድነትን የጌታንና የክርስቲያንን አብሮ መኖርን ይሰጣል ክርስቶስ የማያድርባቸውስ ምን ይሆናሉ ሌላ ሊያድርባቸው ነው ክርስቶስ ወይም ሰይጣን ሊያድርባቸው ግድ ነው።

5. በክርስቶስም ስንኖር ፍሬ ማፍራት አለብን። ቅርንጫፍ በዛፍ ላይ እስካለ ድረስ ፍሬ ማፍራት አለበት። "በኔ ጸንታችሁ ኑሩ እኔም በአላንት እኖራለሁ ጫፍ በወይን ግንድ ላይ ካልኖረ ብቻውን ማፍራት እንደማይችል እላንትም በኔ ካልኖራችሁ እንዲሁ ናችሁ። (ዮሐ.15:4)
6. ደግሞ ሕይወት እናገኛለን እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም (ዮሐ. 6:53) ክርስቶስ የሕይወት ምንጭ ስለ ሆነ ከእርሱ ከተለየን ሕይወት የለንም።
ሥጋው ደሙ ይሕይወት መድኅኒት መሆኑ በትክክል ተነግሮዋል ስለዚህ ምእመናኑ ወደ ጌታ ማዕድ በሚገባ ቀርበው የጌታችን የኢየሱስን ሥጋ የበሉና ደሙንም የጠጡ እንደ ሆነ እርሱ በነሱ እነሱም በእርሱ እንደሚኖሩ በርግጥ እናምናለን። እውነት ነው በበላነው ሥጋው በጠጣ ነው ደሙ ሕይውትንና ሕያውነትን ሊሰጠን ከሥጋው ሥጋ ከዋንቱ አዋንት ሆኑ።
7. ሕይወትን ማግኘት ብቻ ሳይሆን በዚህ ሕይወት የማደግ ስጦታም አለን። ጫፍ በግንዱ ጸንቶ ሲኖር የሚያገኝው ሕይወት ብቻ አይደለም የማደግም ኀይል ያገኛል እንጂ። ወደ ጌታ ቀርበን ሥጋውን ደሙን ስንቀበል በጸጋ ለማደግ ታላቁ ርዳታ እናገኛለን። ምግብ ለሰውነት ማደግ እንደሚረዳ እንዲሁም ይህ መንፈሳዊ ምግብ ነፍስን እንድታድግ ይርዳታል። በጸጋ ለማደግ የያንዳንዱ ሰው ተግባር ነው። በጸጋ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዕውቀት ብዙ (2ጴጥ 3:18)

8. በዚህ ዓለም በረሃ የሚደግፈን ኀይል እናገኛለን የእስራኤል ልጆች መናውን በበሉ ጊዜ ያለድካም አርባ ዓመት ምሉ በበረሃ ለመጎዝ ኀይል አገኙ። ክርስቶስም ከመና የተሻለ ሥጋውን ስጠን እንጂ መና አልሰጠንም። አይሁድ አባቶቻቸው በበረሃ መና እንደ በሉ በነገሩት ጊዜ እንዲህ ብሎ መለሰላቸው። ኢየሱስም አላቸው እውነት እውነት እላችኋለሁ ያን እንጀራ ሙሴ ከሰማይ የሰጣቸሁ እይደለም እውነተኛውን እንጀራ አባቴ ከሰማይ ይሰጣችኋል እንጂ። ከስማይም የወረደው ለዓለም ሕይወት የሚሰጥ የእግዚአብሔር እንጀራ ነውና (ዮሐ. 6:32-33)

9. በአዲስ ኪዳን ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆነናል እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር አዲስ ኪዳን እንደሚያቆም ነቢያት በብሉይ ኪዳን ትንቢት ተናግረዋል። "እነሆ ዘመን ይመጣል ይላል። እግዚአብሔር ከእስራኤል አይሁድ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን አከየዳለሁ። አባቶቻቸውን እንደ ተከየድሁበት ኪዳን አይደለም። ከምስር ምድር አዋጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁ ጊዜ ቃል ኪሳኔንም አፈረስሁ። እኔም ናቅኋቸው ይላል እግዚአብሔር። ነገር ግን ይህ ነው የእስራኤልን ቤት የምካየድበት ኪዳን ከዚያች ዘመን በኋላ ይላል። እግዚአብሔር ሕግን በውስጣቸው አሰጣቸዋለሁ በልባቸውም እጽፈዋለሁ እምላክም እሆናቸዋለሁ እርሳቸውም ሕዝብ ይሆኑኛል። ደግሞም ሰው ባልንጀራውን አያስተምርም ሰውም ወንድምም ሰው ባልንጀራውን አያስተምርም ሰውም ወንድሙን እግዚአብሔርን ዕወቅ ሲል ሁሉ ያውቀኛልና ከታናሾቻቸው ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ይላል እግዚአብሔር። ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ። ደግሞም በደላቸውን አለስብም።( ኤር.31:31-34)

በዚህ ጽሑፍ እንደምናየው የመጀመሪያው ቃል ኪዳን የተሠራው እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች እጃቸውን ይዞ ከግብጽ ባወጣቸው ቀን በፋሲካው ደም ታትሞ ነው። አዲሱ ቃል ኪዳን ግን የተሠራ በመስቀል ላይ በክርስቶስ ደም ታትሞ ነው። ስለዚህ ሥጋውን ደሙን ባቆመ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው። "ሁላችሁ ከዚህ ጠጡ ይህ ደሜ ነውና ለአዲስ ሥርዓት።"(ማቴ.26:27-28)

በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደም ስናምን ጽድቅ አግኝተን ያዲሱ ቃል ኪዳን ልጆችና ወራሾች እንሆናለን ደሙንም ስንጠጣ ከዚህ ቃል ኪዳን ጋራ ያለን አንድነት ይታተምና የጸና ይሆናል። ቅዱስ ቁርባን ስንቀበል ለዚህ ቃል ኪዳን ታማኞች መሆናችንን እንመሰክራለን።

10. ስለ እኛ የተቀበለውን መከራና ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በመስቀል ላይ የተፈጸመውን ታላቁን የማዳን ሥራ እናስታውሳለን። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ ባወጣቸው ጊዜ የፋሲካውን በግ አርደው ደሙን በቤታቸው ደጃፍ እንዲረጩት አዘዛቸው። ደሙም ምልክት ይሁንላችሁ እናንተ ባላችሁበት ቤት ሁሉ ደሙንም አያለሁ ካላንተም አልፋለሁ መቅሠፍትም አይሆንባችሁም። እኔ የምስርን ምድር በመታሁ ጊዜ

(ዘፀአ.12:13) ። ያ ደም የሰውን ፍጥረት ሁሉ ላማዳን በመስቀል ላይ ለሚፈሰው ለዚህ ለተከበረው ደም ምሳሌ ነበር።

የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ባርነት ያዳናቸውን የፍቅርን ሥራና ኃይል ሁልጊዜ እንዲያስታውሱት አስፈላጊ ነበር። ስለዚህ ጌታ እንዲህ ብሎ አዘዛቸው። ይህም ቀን መታሰቢያ ይሁናችሁ። ለእግዚአብሔርም በዓል ታደርጉታላችሁ። በልጅ ልጃችሁ የዘለዓለም ሥርዓት በዓል ታደርጉታላችሁ። ይህቺንም ሥርዓት የምትጠብቅ ሁን። በተሠራው ወራት በያመቱ (ዘፀአ.12:14 13:10)

እኛም ደግሞ ከኃጢአት ባርነት ነጻ የወጣንበትን የተከበረውን ደም ሁልጊዜ እንድናስበው ይገባል። ስለዚህ ሥጋውንና ደሙን ለደቀመዛሙርቱ በሰጣቸው ጊዜ እንዲህ አለ ይህንንም ለመታሰቢያዩ አድርጉት(ሉቃ.22:19)

11. መከራውንም ስናስብ ለእኛ ያደረገውን ታላቅ ፍቅሩን እናስታውሳለን "እንዲሁ እግዚአብሔር ዓለሙን ወዶታልና አንድ ልጁን ቤዛ አድርጎ እስኪሰጥ ድረስ በእርሱ ያመነ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት ትሆንለት ዘንድ እንጂ እንዳይጠፋ 1ኛ 3:16)

ፍቅሩንም ስናስታውስ በርሱ ያለን ፍቅር ይበዛል እግዚአብሔርን እንውደደው እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና (ዮሐ. 6:32-33)

12. ለእርሱ ለመመስከር ስጦታ እናገኛለን ይህንንም ኅብስት ስትበሉ ይህንንም ጽዋ ስትጠጡ እሲኪመጣ ድረስ የጌታን ሞት ትመሰክራላችሁ (1ኛ ቆሮ. 11:26) እውነተኛ ሕይወት ሊኖረን ፍሬ ማፍራት አለብን ከክርስቶስ ብርሃን ስንቀበል ያን ብርሃን ሌሎችን ማሳየት አለብን። ክርስቶስም ከጨለማ ወደ ጌትነቱ ብርሃን ሲጠራን ምስጋናውን መግለጥ ይገባናል። 1ኛ ጴጥ. 2:9)

13. ክርስቲያኖች በወንድማማችነት ከሰማያዊ አምላክ ማዕድ ሲካፈሉ በጣም የበለጠ አንድነት ያገኛሉ። እነደ ዐዋቂዎች ሰዎች የሚገባ ፍርድ ብዩ እንግራችኋለሁ። ይህ የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር አንድ አይደለምን? ይህም የምንፈትተው ኅብስት ከክርስቶስ ሥጋ ጋር አንድ አይደለምን? ኅብስቱ አንድ እንደ ሆነ እንደዚሁም እኛም ብዙ ስንሆን አንድ አካል ነን ሁላችንም ካንድ ኅብስት እንቀበላለን"(1ኛ ቆሮ. 10:15-17)

ስለዚህም ሥጋውን ደሙን የማይቀበሉ ከክርስቶስ አካል ብቻ መለየት ሳይሆን ከቅዱሳንም አንድነት ስለሚለዩ ከምእመናን ጋር እውነተኛ ግንኙነት የላቸውም።

ሥጋው ደሙ ማለት ከራሱ ከክርስቶስ ከምእመናን ወንድሞቻችንና በምድር ካለች ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ከሚገኙት ቅዱሳን ከመላእክትና ከሊቃነ መላእክት ከሰማይ ሠራዊት ሁሉ ጋር ቅዱስ አንድነት ማለት ነው። የእግዚአብሔር ማዳን ወደ እኛ የሚመጣው ከወንድሞቻችን ጋራ አንድነት ሲኖረን መሆኑን ምስጢረ ቁርባን ይነግረናል። በእውነት እንደሚረዳው ይህ የአባታችን የእግዚአብሔር ቤተሰብ የጋራ ምግብ ነው እንጂ የያንዳንዱ ሰው ስግደት ሥራ አይደለም።

እዚህ የማዕረግ የዕውቀት የዘርና የመልክ ልዩነት ወደኋላ ይቀራል እዚህ የተማረና ባላገር ያልሠለጠነና የሠለጠነ ግሪክ መስኮብ ግብጻዊ ኢትዮጵያዊና ማናቸውም ሌላው ዘር በዚህ በትልቁ የማዳን ጉዳይ ሁሉም አንድ ናቸው። እያንዳንዱ የሥጋው ደሙ ሥራ በእግዚአብሔር አሳብ እንዳለች አድርጎ የቤተ ክርስቲያንን እርግጠኝነት ያሳስበናል። ይህ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን እንዳለች ሆና ራሷ የሆነውን የአምላክን አሳብና ፈቃድ የበለጠ አድርጋ ስትገልጥ ለንስሓ ለምስጋና ማቅረብና ለመታረቅ ምቹ ጊዜ መሆኑ የታወቀ ነው።

በምሥጢረ ቁርባን ሥጋውን ደሙን ሊቀበሉ ለቀረቡት ምእመናን ከሐዋርያት ከሰማዕታትና ከቅዱሳን ሰማያዊ አንድነት ክፍል እንዲገኙ ጸሎት ይደረጋል። በጌታ ጸሎታና በሰላም መገናኘት ምእመናኑ በቤተ ክርስቲያን የእርስ በርሳቸውን አንድነት ያስታውሱታል ያጽኑታልም። በራሱም በሥጋወ ደሙ ምእመናኑ በላይኛው ክፍል በሆነው ራት ሐዋርያት ከጌታ እጅ የተቀበሉትን ዕይነት ስጦታ ይቀበላሉ። ስለዚህ

ከክርስቶስ ጋራ አንድነት እንዳለን የምናስረዳው ወንድሞቻችንን በመውደድ ስለ ሆነ የወንድሞች ፍቅር በውስጡ ሳይኖር ከጌታ ራት የሚሄድ ማናቸውም ሰው ምንም አልተቀበለም የነበረውም በከንቱ ነው።

14. በመጨረሻ የዘለዓለም ሕይወት እናገኛለን። ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው እኔም በኋላኛዪቱ ቀን አስነሣዋለሁ። (ዮሐ. 6:56) አሁንም የተወደድህ ወዳጄ ሆይ ለትንሽ ጊዜ በጸጥታ እንድትአስብ በእግዚአብሔር ምሕረት እለምናለሁ። የዘለዓለም ሕይወት ምን ማለት እንደ ሆነ ታውቃለህ? እውነተኛ የዘለዓለም ደስታ ነው። እርሱም "ዓይን ያላየው ጆሮም ያልሰማው በሰው ልቦና ያልታሰበ ክብር ነው"። (1ኛ ቆሮ. 2:9)

ዘወትር ከጌታ ጋራ ሆኖ "በበጉ ሰርግ ራት" መደሰት ነው። (ራዕይ 19:9) ግን በጌታ ራት እዚህ ደስ የማይላቸው እዚያ በራቱ ደስ ሊላቸው አይችሉም። የዘለዓለምን ሕይወት ማጣት ምን እንደሚያመጣ ታውቃለህ? ላንድ ሰዓት ላንድ ዓመት ለሚሊዮን ዓመት ሳይሆን ለዘለዓለም ስለ ማይጠፋ እሳት ባሰበ ጊዜ እንዲህ አለ "ማነው ከእኛ ከምታቃጥል እሳት ጋራ መቀመጥ የሚችል። ማነው ከእኛ ለዘለዓለም ከምትነድ እሳት ጋራ መኖር የሚችል"። (ኢሳ. 33:14)

ይህን የዘለዓለም ሕይወት ማግኘት አትፈልግም? ምንም አታወጣበትም። "እላንተ የተጸማችሁ ሁሉ ወደ ውሃ ኑ ብርም የሌላችሁ ሁሉ ግዙ ብሉም ኑ ያለ ብርም ግዙ ያለመግዣም ጠጅና ወተት ለምን ብር ትመዝናላችሁ እንጀራ ላይድለው ድካማችሁስ ለማያጸግባችሁ። ነገሬን ስሙ በረከትንም ብሉ ሰውነታችሁም በድንዳኔ ደስ ይላታል በጆሮአችሁ ወደኔ አድምፁ ወደኔም ቅረቡ ስሙ ሰውነታችሁም ትድናለች የዘለዓለም ቃል ኪዳን አከየዳችኋለሁ የታመነችውን የዳዊትን ጸጋ"( ኢሳ.53:1-3)

## ምዕራፍ 3

## ሥጋውን ደሙን የሚገባው ማነው የሚቀበለውስ ምን ያህል ነው?

ቤተ ክርስቲያን ወይም መጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የሆኑ ሁለት እውነተኛ ነገሮች ያስተምረናል።
ሀ) በክርስቶስ አካል ሕያዋን ወገኖች ለመሆን እውነተኞች ክርስቲያኖች ሁሉ ቅዱስ ቁርባን መቀበል ይገባቸዋል። ይህ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ለቀሳውስትና ለዲያቆናት ብቻ አልተሠራም። በሥጋው በደሙ እዚህ እውነተኛ ሕይወት እዚያ የዘለዓለም ሕይወት የምናገኝ ከሆነ ሁላችንም መቀበል ያስፈልገናል።

ይህንን ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ባቆመ ጊዜ ክርስቶስ ምእመናን ሁሉ መቀበል እንደ ሚገባቸው አዘዘ "ጽዋውንም ተቀብሎ አመስገነ ሁላችሁ ከዚህ ጠጡ ብሎም ሰጣቸው (ማቴ.26: 27)።

ለ) ደግሞ ሳያሳታጉሉ ሊቀበሉት ይገባል ቅዱስ ቁርባን ለነፍስ እውነተኛ ምግብ እንደሚሰጥ እናውቃለን። በዓመት አንድ ጊዜ ወይም ባሥር ዓመት አንድ ጊዜ ወይም በዘመነ ዕድሜ አንድ ጊዜ እንመገባትን? ከክርስቶስ ጋራ መገናኘት የሚገባን እንዲያው በዘፈቀደ ነው?

እውነተኛ ምእመናን ሥጋውን ደሙን በየሳምንቱ አንድ ጊዜ መቀበል አስፈላጊያቸው ነው። የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ትእዛዝ በደንብ ለመፈጸም በጣም ጠንቃቃ ነበረች "በሐዋርያትም ትምህርትና ባንድነት እንጀራም በመባረክና በጸሎት ጸንተው ኖሩ።" (የሐዋ.2:42)

ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ይህንን አገልግሎት በደንብ በመፈጸምና ለክርስቲያኖች ሁሉ ምሥጢረ ቁርባንን በየሳምንቱ በመስጠት በመጀመሪያዎቹ መቶ ዓመታት በጣም ጠንቃቃ ነበረች። በመሐከለኛውና በአሁኑ ጊዜ በክርስቲያን ሃይማኖት ከሆኑት ከሚያሳዝኑ ሁኔታዎች አንዱ የቀድሞው ምሳሌ መጥፋት ነው። ቁርባን በሕዝብ በኩል ችላ ተብሎ አብዛኛውና ጊዜ የሚቀበለው ያው ቁርባኑን የሚሰጠው ብቻ ነው። ምእመናኑ ለግል አገልግሎት የተጠመደ እያንዳንዱ ሰው የተሰበሰበበት ጉባኤ እንጂ እንደ አንድ አካል ሆነው

አልታዩም።

ይህ ምሥጢረ ቁርባን የተመሠረተው ግልጥ በሆነው በክርስቶስ ትእዛዝ ነው። በተቻለን መጠን ለእግዚአብሔር ትእዛዝ መታዘዝ ዘወትር ግዴታ ስላለብን ምስጢረ ቁርባንም ለሰው ከእግዚአብሔር የመጣ ምሕረት ስለ ሆነ ይህንን ታላቅ ምሕረት ማለት የጌታን ራት በተቻለ መጠን አዘውትሮ መቀበል የያንዳንዱ ክርስቲያን ተግባር ነው።

ቤተ ክርስቲያን ስታስተምር ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ በየሳምንቱ ሥጋውን ደሙን መቀበል እንደሚገባው ታዝዛለች። "በጸሎት መጨረሻ መጀመሪያ ኤጲስ ቆጶስ ሥጋውን ደሙን ይቀበል። ቀጥሎ ቀሳውስትና ዲያቆናት ከነሱም በኋላ መላው ሕዝበ ክርስቲያን" (ረስጣብ፤ 52)

ቅዳሴው ሲፈጸም መጀመሪያ እርሱ ሥጋውን ደሙን ይቀበል። ከዚያ በኋላ እንደ ቤተ ክርስቲያንቱ ሥርዐት ለሁሉም ያቀብላቸው" (ድድስቅያል 36)። ሥጋውን ደሙን የማይቀበሉት ሲጠየቁ በማናቸውም መንገድ የማይመስል ምክንያት ይሰጣሉ።

1. አንዳንዶች ኃጢአተኞች ስለሆኑ ይህንን ቁም ነገር የሆነውን ምሥጢረ ቁርባን ለመቀበል የተገባን አይደለንም ይላሉ። ሁላችንም ኃጢአተኞች መሆናቸውን እርግጥ ነው። ደግሞም ከእግዚአብሔር ስጦታዎች ለማናቸውም ሁላችንም የተገባን አለመሆናችን እርግጥ ነው። ግን ይህ ማለት ከኃጢአታችን ከሚያነጻን ከደሙ ምንጭ መራቅ ይገባል ማለት ነው? የጤናን ሕግ ዘወትር ይተላለፋልና በሽተኛ ከማናቸውም ሕክምና ይራቅ ማለት ነው? ክርስቶስ የመጣው ወደ ማን ነው? ለዚህ ጥያቄ ራሱ መልስ የሰጣል። "ኢየሱስም በሰማ ጊዜ አላቸው። የታመሙ እንጂ ጤነኞች ባለ መድኃኒትን አይሹትም። ነገር ግን ሂዱ ዕወቁትም ይህ ምንድር ነው ኃጥአንን ወደ ንስሓ ልጠራ መጣሁ እንጂ ጻድቃንን ለመጥራት አልመጣሁምና" (ማቴ.9:12-13)

ኃጢአተኛ መሆንህን ከተረዳኸው መልካም ምልክት ነው። ሕሊናህ ገና እንደ ነቃ መሆኑንና አሁንም ገና ኃጢአትን የምትጠላ መሆንህን ያሳያል። ወደ መሐሪው አባትሕ ፊጥነህ ተመለስ እርሱ አንተን እንዳለህ ሊቀበልህ ዝግጁ መሆኑን ዕወቅ።

2. ሌሎችም ምሥጢረ ቁርባንን ከተቀበልን በኋላ እንደ ገና እንወድቃለን ብለው ይፈራሉ። በኃጢአተኛና በኀጢአት በሚኖር ሰው መሐከል ታላቅ ልዩነት እንዳለ ማወቅ ይገባናል። ይህም እውነት ለመሆኑ ቀጥሎ ያለው ማስረጃ ገልጦ ያሳየናል። ሕፃናት ሁሉ ልብሳቸውን ለማሳደፍ ግድ አለባቸው። ግን በጣም ንጹሕ በሆነ ቤተሰብ በሚኖር ሕፃንና በጣም ቁሻሻ በሆነ በተሰብ በሚኖር ሕፃን መሐከል ታላቅ ልዩነት አለ። ሕፃናት በመሆናቸው ሁለቱም ለመቆሸሽ ግድ አለባቸው። ይሁን እንጂ የመጀመሪያው ሕፃን ልብሱ ወዲያው ትንሽ ሲቆሸሽ እንድታነጻለት ወደ እናቱ ፈጥኖ ይሄዳል። ሁለተኛው ግን በልብሱ ላይ ምንም ቆሻሻ ቢከማችበት አይሰማውም።

ታላላቆች ቅዱሳን እንኳን ሳይቀሩ ሰው በመሆናችን ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን። ወደ ኃጢአትም ለመውደቅ ግድ አለብን። የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት ግን ወዲያው በኃጢአት ሲወድቅ ልብሳቸውን በክርስቶስ ደም እንዲአነጻላቸው ፈጥነው ወደ ሰማያዊ አባታቸው ይሄዳሉ። ቅዱስ ዮሐንስ በመጀመሪያዩቱ መልእክቱ እንዲህ አለ "በርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአት አይሠራም። (በኃጢአት አይኖርም)። ኃጢአት የሚሠራ ሁሉ አላየውም አላውቀውምም" (1 ዮሐ. 3:6) ወዲያውም ይህነን ካለ በኋላ ልጆቼ ሆይ ይህቺን ነገር እጽፍላችኋለሁ ኃጢአት እንዳትሠሩ ከላንተም ማንም ኃጢአት ቢሠራ ከአብ ዘንድ አማላጅ አለን ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ (1 ዮሐ. 2፡1)

ስለዚህ በመውደቅ አትፍራ ብትወድቅም ተነሣ ሰዎች የሚፈፈድባቸው በኃጢአት በመኖራቸው ነው እንጂ ሰባት ጊዜ ይወድቃልና ይነሣማል ኃጢአተኞች ግን ለጥፋት ይወድቃሉ (ምሳሌ 24:16) አንቺ ጠላቴ በኔ ደስ አይበልሽ ብወድቅ እነሳለሁና (ሚክ.7፤8)። ለተፈጥሮህ የሚያስጠላ ሆኖ ስለምታገኘው ወደ እግዚአብሔር የቀረብህ ያህል ኃጢአትን የበለጠ እንደምትጠላ ዕወቅ። "ከእግዚአብሔር የሚወለድ ሁሉ ኃጢአት አይሠራም። ዘሩ ጻንቶበታልና ኃጢአትም ይሠራ ዘንድ አይችልም ከእግዚአብሔር የተወለደ ነውና" 1ኛ ዮሐ 3፡9።

3. እንዳንዶች በየሳምንቱ ሥጋውን ደሙን መቀበል እንደ ልማድ ይሆንና ኀይሉ ይጠፋል ይላሉ። ይህ የበቃ ምክንያት ሊመስል ይችላል። እንደ እውነቱ ግን ሊሆን አይቻልም። ሥጋው ደሙ እንደ ጥልቅ ጸሎት አይደለምን? በቀን በቀን ብቻ ሳይሆን በየጊዜው እንድንጸልይ አልታዘዝንምን? ጸሎት እንደ ልማድ እንዳይሆን በማለት ዘወትር ልንጸልይ አይገባንም ማለት የበቃ ምክንያት ነውን? ወደ እግዚአብሔር የቀረብን ያህል የበለጠ ደስ እንደሚለንና ከበረከቱም ለመቀበል የበለጠ ፈቃደኞች እንደምንሆን አይጠራጠርም።

4. አንዳንዶቹም ወንዶች ምሽቶቻቸውን ሴቶች ባሎቻቸውን አስቀድሞ ለውጠው ይሆናል ብሎ በመፍራትና በመጠርጠር ትልልቆች የሆኑትን ሌላ ርኩስጠ ሳያውቁባቸው ትልልቆች መሆናቸውን በመመልከት ብቻ ምሥጢረ ቁርባን እንዲቀበሉ ሊፈቀድላቸው አይገባም የሚሉ ይገኙ ይሆናል። ሥራቸው የጠፉትን በጎች መፈለግ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን ቀሳውስት ይህነን ምክንያት ከቶ ሊቀበሉት አይገባም። ባሎችዋ ካልነበሩ ወይም ቢያንስ ቢያንስ ጥቂቶች ባሎችዋ ከነበሩ ከስድስት ሰዎች ጋራ የኖረችዋ የሰማርያ ሴት የሕይወት ወሃ ተሰጣት እንጂ በጌታ ዘንድ አልተነቀፈችም። ጌታም ስለ ተቀበላት ለምትኖርበት ከተማ መዳኛ ሆነች። ማርያም መግደላዊትን በምንዝርና የተያዘችዋን ሴት በመስቀል ላይ የነበረውን ሽፍታ ቀራጮችንና ኃጢአተኞችን ሁሉ ጌታ ስለ ተቀበላቸው ለንስሓ ጊዜ አገኙ።

## ምዕራፍ 4
## <u>መዘጋጀት</u>

ሳይጠነቀቁ በግድየለሽ አሳብ ወደማናቸውም መንፈሳዊ አገልግሎት መግባት አይገባም። የአገልግሎት ሥራ የተከበረ እንደ ሆነ ያህል ለዚሁ መዘጋጀት ይህኑ ያህል አስፈላጊ ነው። ሰዎች ወደ ንጉሥ ግብዣ በተጠሩ ጊዜ በሚስማማ በአክብሮት ምልክት እንዲታዩና እንዲሁም ጠሪዎቹም የተቻለ ያህል የሚደሰቱበትንና የሚከበሩበትን ሁኔታ እንዲያደርጉ የተለመደው የአኗኗር ሥርዐት ያስተምራል። ወደ ነገሥታት ንጉሥ አንድነት በተጠሩ ጊዜማ ክርስቲያኖች እርሱን ደስ ለማሰኘት ከዚህ የበለጠ እንዲያደርጉ እንደ ምን አያስፈልጋቸውም?

በዚህ አገልግሎት በልዩ መንገድ ወደ አንድ ልዩ ደረጃ ከእውነተኛው ከክርስቶስ ፊት የምንቀርብ መሆናችንን ድሉ መጀመሪያ ከታወቀበት ከላይኛው ክፍል ጋራ ይህ አገልግሎት የሚጠብቀውን ቀጥታ ግንኙነት አሁን የድሉ ተካፋይነታችንን ስንገነዘብ ይህ ሁሉ አንድነት ሆኖ ለዋናው አገልግሎት ወደምንዘጋጅበት መንገድ ይጠራናል። (ከቅዱስ ቁርባን መካፈል ቀላል ነገር አለመሆኑ አይጠራጠርም። አስቀድሞም ኋላም ታላቅ መዘጋጀት ያስፈልጋል። ቅዱስ ጳውሎስ አለ "ስለዚህም ይህንን እንጀራ የሚበላ ሁሉ የጌታንም ጽዋ የሚጠጣ ሳይገባው በጌታ ሥጋ በደሙም ዕዳ ይገባል። ሰውም ራሱን ይፈትን እንዲሁም ይህነን እንጀራ ይብላ ይህነንም ጽዋ ይጠጣ ሳይገባው ግን ቢበላ ቢጠጣም ለራሱ ኩነኔ ይባላል ይጠጣልም። የጌታን ሥጋ ባያውቅ (1ኛ ቆሮ. 11፤27-29)

## ይህ መዘጋጀት ምን ማለት ነው?
## 1/ <u>ሥጋውን ደሙን ከመቀበል በፊት።</u>

ሀ/ ራስን መመርመር "ሰውም ራሱን ይፈትን እንዲሁም ይህነን እንጀራ ይብላ ይህነንም ጽዋ ይጠጣ። (1ኛ ቆሮ. 11፤28) "ራሳችሁን መርምሩ በሃይማኖት ቆማችሁ እንደ ሆነ ራሳችሁን ፈትኑ 2ኛ ቆሮ. 13፤5) በእግዚአብሔር ፊት በትሕትና ወድቀህ እንዲህ ብለህ ለምነው "አቤቱ መርምረኝ ልቤንም ፈትነኝ አሳቤንም ዕወቅ ጉስቁልናም መንገድ እንዳለብኝ እይ የዘለዓለምንም መንገድ እንዳለብኝ እይ የዘለዓለምንም መንገድ ምራኝ" (መዝ. 139:23-24)

ትክክለኛ ምሳሌ መሆን ይሚችል ስለሌለ ራስህን ደኅና አድርገህ ለማወቅ ሕይወትህን ከሌሎች ጋራ አታመዛዝን። "ነገር ግን የአዳም ልጆች ሁሉ ከንቱ ናቸው አዎን የሰው ልጆችም ሐሰተኞች ናቸው።

እርሳቸውስ ሁላቸው በሚዛን ተመዝነው ከምናምን የቀለሉ ናቸው። (መዝ. 62:9) እውነተኛው ምሳሌአችን እንድንከተለው ምሳሌ የተወልን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (1ኛ ጴጥ. 2፣21 ) ከቅዱሳን ቅዱስ ወደሆነው ነፍስህን አንሣና ከሁሉ ከፍ ያለውን ቅድስና ለጥቂት ጊዜ ተመልከት። በእግዚአብሔር ፊት ብርሃን እነዚህን ጥያቄዎች ራስህን ጠይቅ። በየቀኑ ያለማቋረጥ ትጸልያለህን? ጸሎትህ ጥልቅ የሆነ የመንፈስ ጸሎት ነው ወይስ ልብን የማይነካ የአፍ ጸሎት? ስትጸልይ በእግዚአብሔር ፊት እንዳለህና እርሱም እንደሚሰማህ ታውቃለህ? ከቤተሰብህ ጋር ጸሎት ዘወትር ታደርጋለህ።

ለነፍስህና ለሌሎችም ሰዎች ነፍስ ምግብ ለማግኘት ዘወትር መጽሐፍ ቅዱስ ታጠናለህ? መጽሐፍ ቅዱስ ስታጠና እያንዳንዱ ቃል የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ታስተውለዋለህ? ከቤተሰቡ ለያንዳንዱ ሰው የሕይወት ምግብ ለመስጠት ለቤተሰብህ በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱስ ታነባለህ?

በቤተሰብህ ለያንዳንዱ ሰው ኀላፊ እንደሆንህ ታውቃለህ? አንተና ቤተሰብህ የክርስቶስ እንደሆናችሁ እርግጠኛ ነህ? ከእግዚአብሔር ጋራ ያለህ ግንኙነት የማያቋርጥና ጠንካራ ነው ወይስ በእግዚአብሔርና ባንተ መካከል በኃጢአትህ ታላቅ የሚለያይ ግድግዳ ሠርተሃል "ነገር ግን ኃጢአታችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መሐከል ለየች። ክፋታችሁ በደም ረክሳለችና ጻታችሁም በበደል ከንፈራችሁ ሐሰት ተናገረ። መላሳችሁም ኃጢአት ይናገራል። () የአካልህ ክፍሎች ሁሉ ንጹሖች ናቸው? እጆችህ ንጹሖች ናቸው? ዓይኖችህ ንጹሖች ናቸው? አንደበትህ ንጹሕ ነው? ሐሰት መናገር አለመደምን? አሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት ወደምትቃጠል ባሕር ነው? (ኢሳ. 59፤2-3) ይህን ታውቃልህን "ምናምን  ነገር ሁሉ ሰዎች የሚናገሩበት ምላሽ ይስጡበታል። በፍርድ ቀን ከነገርህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከነገርህም የተነሣ ይፈረድብሃልና።
(ራእይ 21፤8) ይህን ታውቃልህን?

**ከምታውቀው ከያንዳንዱ ሰው ጋራ ትክክለኛ ግንኙነት አለህን?**
እንደ እግዚአብሔር ልጅ ሆነህ ትኖራለህን? በእግዚአብሔር ልጅነትህ መብት ሁሉ ትደሰትበታልህን? በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በተደበቀው የተስፋ ሀብት ትደሰትበታለህን? ስለ አሁኑና ስለ አለፈው ሕይወትህ በጥልቅ አሳብ ወይም ቢያንስ ቢያንስ ወደ ፊት ምን መሆን እንደሚገባህ አስብ። የጠፋው ልጅ ያለበትን መጥፎ ሁኔታ በተረዳ ጊዜ ካሁኑ ሁኔታው ጋራ ሲመዛዘን ባባቱ ቤት እንደ ልጅ ሆኖ የነበረበትን የቀድሞ ሁኔታ አስበና ካባቱ አገልጋዮች ከአነስተኛው በታች ሆኖ በመገኘቱ በጣም አዘነ። "ወደ ልቦናው ተመለሰና አለ። ስንት ናቸው የአባቴ አገልጋዮች እንጀራ የሚተርፋቸው እኔ ግን ከዚህ በረኀብ እሞታለሁ" (ሉቃ 15፡17)

**ኃጢአተኛ መሆንህን ከተረዳህ አንድ ነገር ለማድረግ በአሳብህ ቁረጥ።**
ለ/ <u>አሳብን መቁረጥ</u> መዘጋጀት ማለት ደኅና ሁነህ እስክትዘጋጅ ሕይወትህ በሙሉ ንጹሕ ሆኖ ወደ ጌታ ራት ለመቅረብ የተገባህ እስክትሆን ድረስ ሥጋውን ደሙን ሳትቀበል መቆየት ይገባሃል ማለት አይደለም። ኃጢአት የተመላህ መሆንህን ካወቅኸው እግዚአብሔር በቶሎ ንስሓ እንድትገባና ንጹሕ ሆንህ ለመኖር አሳብህን እንድትቆርጥ ይፈልጋል። የጠፋው ልጅ አዲስ ልብስ ለመግዛት ወይም ራሱን ንጽሕ ለማድረግ እስትችል አልቆየም። እንደዚያው እንደ ነበረ ሆኖ ሂዶ ኃጢአተኛ መሆኑን ተገንዝቦ ልጅ ለመባል የማይገባው መሆኑን የበለጠ ስለ ተረዳው አባቱ ካገልጋዮቹ እንደ አነስተኛው አድርጎ ቢቀበለው እንደ ታላቅ ሞገስ ቆጠረው "ልነሣና ወደ አባቴ ልሂድ (ይህ አሳብን መቁረጥ ነው) ልበለውም አባቴ ሆይ በሰማይ በፊትህም በደልሁ ደግሞም አይገባኝም ልጅህ እባል ዘንድ ከባሮችህ አንዳንዱ አድርገኝ" (ሉቃ. 15:18-19)

ሐ/ ለማድረግ የቆረጥኸውን በቶሎ ፈጽመው። ኃጢአተኛ መሆንህን ማወቅና አሳብን መቁረጥ ብቻ በቂ አይደለም። ገሃነም በነዚያ መልካም አሳብ ባላቸው ተመልቶአል። አንተ ግን በሚመጣው ወር ነገ ከቶውንም ዛሬ ሳይሆን አሁን ተነሣና እንደ ነበርህ ሆነህ ወደ ሰማይዊው አባትህ ሂድ። አሁኑን ወደርሱ ሩጥ ነገ ወይም ካንድ ሰዓት በኋላ የተመቸ ጊዜ አታገኝም ይሆናል።

የጠፋው ልጅ "ልነሣና ወደ አባቴ ልሂድ ባለ ጊዜ ስለ እርሱ እንደሚነገረው ወዲያውኑ ተነሥቶ ሄደ እንጂ አንዲት ደቂቃ እንኳን አላመነታም። በዚህ ሁኔታ ምን ትምህርት አገኘ ገና ሩቅ ሳለ (እርሱ አባቱን ሳያየው) አባቱ እርሱን አየውና ራርቶለት (ምንም የሸመገለ ቢሆን) ሮጦና ባንገቱ ላይ ወድቆ ሳመው። ለአገልጋዮቹም

እንዲህ አላቸው ደጎና ልብስ እምጡና አልብሱት ቀለበትም በጣቱ አድርጉለት ጫማም በእግሩ የሰባም ፍሪዳ አምጡና እረዱ እንብላና ደስ ይበለን።

ቸሩ የሰማዩ አባትህ ላንተ ሊያደርግልህ የሚወደው ልክ እንደዚህ ነው። ወደ እርሱ ከመቅረብህ አሰቀድሞ ይመለከትሃል። ያቅፍሃል ደጎና ልብስ ያለብስሃል ወደ ተሻለ ሁኔታ ይመልስሃል። የተከበረም ድግስ ማለት የተከበረ ሥጋውንና የተቀደሰ ደሙን ያዘጋጅልሃል።

አሁን ወደርሱ ትሄዳለህ "ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ይጠብቅሃል እነሆ እኔ በደጅ ቆሜያለሁ ደጅም እመታለሁ ማንም ድምፄን ሰምቶ ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ ከርሱም ጋራ ራት እበላለሁ እርሱም ከኔ ጋራ" (ራእይ 3:20) ደጁን ትከፍታለህ? አንተ ከጌታ ጋራ ጌታም ካንተ ጋራ ራት ለመብላት ትወዳለህ ሁሉ ነገር ተዛጋጅቷል። የጌታ ራት ተዘጋጅቷል።

## ጸሎት

ስማያዊ አባት ሆይ ኃጢአተኞችን ሁሉ ወደ ንስሐ ስለምትጠራ እናመሰግንሃለን። ያመነበት ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲያገኝ እንጂ እንዳይጠፋ በማለት አንዱን ልጅህን አሳልፈህ እስክትሰጥ ድረስ ዓለምን ስለወደድህ እናመሰግንሃለን በሰማይም በፊትህም እንደ በደልሁ ዐውቃለሁ አሁንም ኃጢአቴን ይቅር እንድትል ወደ አንተ እመጣለሁ። ወደ ኃጢአትም እንዳልመለስ እርዳኝ ፈጽምህ ልታድነኝ የምትችል አንተ መሆንህን አምኜና የምሰጥህንም እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ ልትጠብቀው የምትችል መሆንህን ተረድቼ ራሴን ላንተ እሰጣለሁ። ልቤን አንጻና ለቅዱስ መንፈስህ መቅደስ እንዲሆን አዘጋጀው። ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ስቀርብም ሥጋህንና ደምህን የተገባኝ ሁኜ እንድቀበለው አድርገኝ።

## የቅዱስ ባስልዮስ ጸሎት

አባት ሆይ እንለምንሃለን ወደ ፈተና አታግባን። ከስንፍና ሥራዎችን እነዚህን ከመሰሉት ሁሉ አድነን። ክፋትም እንዳይነግሥብን ጠብቁን ፈተናንና በውስጣችን ያለውን ክፉ ፍትውቱንና ወደ ኃጢአት ይሚመራንን አሳብ ሁሉ ከኛ አውጥተህ ጣል ሁሉን የምትችል አምላክ ሆይ መላእክት ሊያዩት የተመኙትን ታላቁን ምሕረትህን ለኛ ስላዘጋጀህ እናመሰግንሃለን በቅዱስ መንፈስህ ተመልተን በእውነተኛው እምነትህ ጸንትንና በእውነተኛው ፍቅር ተመልተን ዘወትር ክብርህን እንድንገልጽ ሁላችንን እንድንታነጸንና ከአምላካዊ ቅዱስ ምስጢርህ ስንካፈል ካንተ ጋራ አንድ እንድታደርገን እንለምንሃለን። የዓለምን ኃጢአት የተሸከምህ ጌታ ሆይ ይቅር ባይ አምላክ ጸጋ የተመላህ ለቁጣ የዘገየህ ባለታላቅ ቸርነትና እምነት ነህና ስለ ኃጢአት ይቅርታ የባሮችህን ንስሓ ተቀበል (ዘፀአ.34:6) ቸርና ሰውን የምትወድነህና በንግግር ወይም በሥራ የሠራነውን ኃጢአት ይቅር በለን የኃጢአትን ማሰሪያ ሁሉ ቁረጥ ከማናቸውም ክፋት እንድንሸሽ ጥበብና ኃይል ስጠን ዘወትር ፈቃድህን ለመፈጸም እርዳን ስጠን ዘወትር ፈቃድህን ለመፈጸም እርዳን በመንግሥት ሰማይ ስማችንን ከቅዱሳን ሠራዊትህ ጋራ ጻፍ በጌታችን በኢያሱስ ክርስቶስ አሜን።

## (2) ሥጋውን ደሙን በመቀበል ጊዜ

ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ወደ ቤተክርስቲያን በሄድህ ጊዜ ከሁሉ ቁም ነገር ወደ ሆነ ምስጢር መቅረብህን ማወቅ አለብህ። አሳብህን ሁሉ በአገልግሎቱ ላይ አከማች እግዚአብሔር ልብህን እንዲያነጻው ለመንፈስ ቅዱስ መቅደስ ለመሆን እንዲአዘጋጀውና የተገባህ ሆነህ ሥጋውንና ደሙን ለመቀበል እንዲረዳህ ለምን።

## የዮሐንስ አፈወርቅ ጸሎት

ከጠቢባንና ከዐዋቂዎች የተሠረውን ነገር ለእኛ ለሕጻናት ገልጠሃልና ነቢያትና ነገሥታት ለማየት ተመኝተው ሳያዩት የቀሩትን ነገር ሰጥተኸናልና ጌታ ሆይ የስጦታህ ባለጸግነት የማይነገርና ከአሳባችንም በላይ ነው። እኛን ላማንጻት ይህነን የተሠወረ የመሥዋዕት ምሥጢር ባቆምህ ጊዜ ሥጋ በመልበስህ ይህነን ሰጠኸን። ይህ መሥዋዕት በኦሪት ደም ወይም በሥጋ ጽድቅ አልተሠዋም። ግን በጉ መንፈሳዊ ነው። ወቅለምቱም ምንም የሚዳሰስ ባይሆን የሚናገር ነው። ስለዚህ ስሙን የምትወድ ሆይ ከንፈራችንን እንድታነጻ ልባችንን እንድታጥብ አሳባችንን ከማናቸውም ሥጋዊ ፍትወት እንድታጠራልን እንለምንሃለን። የመንፈስ ቅዱስህን

ስጦታ ላክልን ወደ ፍርድ እንድንወድቅ ሕያዉ ከሆነ ከሰማያዊ ጸጋህ ለመካፈል የተገባን አድርገን ከሰማያዊ ጸጋህ ለመካፈል የተገባን አድርገን። ክብርና ምስጋና በምንሰጠው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በአንተና በመንፈስ ቅዱስ አሜን።

የቅዱስ ባስሎዮስ ጸሎት

የሕይወት መስፍን ሆይ የትውልድ ሁሉ ንጉሥ የእግዚአብሔር አብ ቃል ጌታችን አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ የወረደ እውነተኛ እንጀራ ለሚቀበለው ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ወደ ፍርድ ሳንወድቅ የተቀደሰ ሥጋህንና የተከበረ ደምህን ለመቀበል የተገባን እንድታደርገን እንለምንሃለን። ከቅዱስ ምሥጢራትህ ስንካፈል ለዘለዓለም ካንተ ጋራ እንሁን ባርከንም። ካንተ ጋር አንድ አካል አንድ መንፈስ እንድንሆን በቅዱስ ሥጋህና በክቡር ደምህ ለነፍሳችን ለሥጋችንና ለመንፈሳችን ቅድስና ለበደላችን ለኃጢአታችን ይቅርታ ለመቀበል ሁላችንም የተገባን እንሁን። ላንተ ለቸሩ አባችህና ለመንፈስ ቅዱስ ለዘለዓለም ክብር ይሁን አሜን።

## (3) ሥጋውን ደሙን ከመቀበል በኋላ።

የአምላካችን የተቀደሰ ሥጋና የተከበረ ደም ከተቀበልህ በኋላ ይህንን ታላቅ መብት ስለሰጠህ ልታመሰግነውና ወዲያውም ከርሱ ጋራ ያለህ ግንኙነት እንዳይቋርጥና ከክፉ እንዲጠብቅህ ልትለምነው ይገባሃል።

የቅዱስ ባስልዮስ ጸሎት

ዐይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን ወደ ሰውም ልብ ያልገባውን ለኛ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ ሕፃናት ገልጠሃልና ማናቸውንም መልካም ነገር ሁሉ የሰጠኸንና ከሰማያዊው ሕያው ምሥጢርህ ለመቀበል ዛሬ የተገባን ያደረግኸን ሰውን የምተወድ ጌታ ሆይ እናመስግንሃለን። አሁን በፊትህ ይሚሰግዱትና የባሮችህን ልብ እንድትመላ እንለምንሃለን በማናቸውም መልካም ሥራ ሁሉ ርዳቸው ከማናቸውም ምድራዊ ክፉ አሳብ አእምሮዋቸውን መልስ እንደ ሕያዋን ሆነው እንዲያስቡ ሕያዋን እንድታደርጋቸውና አሳባቸውን በአምላካዊ ነገር እንዲያጸኑ ርዳቸው "እግዚአብሔር መድኃኒታችን ማረን። እያልን እኛን ሕዝበ ክርስቲያንህ ሁሉ በምንልምነው ባንዱ በተወደደው ልጅህ በጌታችን በአምላካችን መድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አሜን።

የቅዱስ ጎርጎርዮስ ጸሎት

ስለ እኛ ራስህን መሥዋዕት አድርገህ እስክትሰዋ ድረስ ወደኸናልና የአብ እውነተኛ ቃል ክርስቶስ ጌታ ሆይ እናመሰግነሃለን በግርፋትህ ፈወስኸን በቁስልህም አዳንኸን አሁን ልንቀበለው የተገባን ባደረግኸን በቅዱስ ሥጋህና በተከበረው ደምህ ሕይወት ስጠኸን በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ባርክን ሁሉን በሚችል ክንድህ ጠብቀን በሃይማኖታችን ባንተ እንጽና ነፍሳችን ሥጋችንና መንፈሳችን በንጹሕ እንዲጠበቁ አድርግ። ክርስቶስ ጌታችን ሆይ ልንወርሳት ተስፋ የምናደርጋት መንግሥትህ ንጽሕትና ክብርን የተመላች ስለ ሆነች በፊትህ ፍጹማን እንድንሆን ርዳን ለስምህ ዘለዓለም ክብር ይሁን አሜን።

የቅዱስ ቁርሎስ ጸሎት

የሞት ፍርድ ተፈርዶብንና በኃጢአት ርኩሰት ሰጥመን ሳለን ለሰማይ አለቆችና ሥልጣናት ጥበብህን ለመግለጥ ለኛ ነጻነት ሰጥተህ ከዚህ ከሰማያዊ ህያው ምግብ እንድንቀበል ስላደረግኸን ካለፈው ትውልድ ሁሉ የተሰወረውን ይህን ምሥጢር ስለገለጥህልን ሰውን የምትወድ ጌታችን አምላካችን ሆይ ስላደረግህልን በጎ ሥራ ሁሉ ምን ምስጋና እናቀርብልሃለን። (መዝ. 116:12) እንዴት ያለ ቸርነትና ምሕረት ነው እንዴት ያለ ታላቅ ፍቅርና ቸርነት ነው እንዴት ያለ ያባትነት መጠበቅ ነው በረከቶችህ ሁሉ በከንቱ ተሰጡ እንጂ ለነሱ ወረታ ሊመለስላቸው አይቻልም ከማለተ በቀር ምን ውለታ እንመልሳለን። ክብርና ምስጋና ለዘለዓለም ላንተ ይሁን አሜን።

**ምስጢረ ቍርባን**

ከቄስ ማርቆስ ዳውድ
አዲስ አበባ 1944
በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ።